# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)

ግንቦት ፲፪ ቀን ፪ ሺህ ፩ ዓ. ም
May 20, 2009

**ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) አመራር ምክር ቤት የተሰጠ መግለጫ**

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ከግንቦት ፮ እስከ ፱፣ ፪ ሺህ ፩ ዓ. ም (May 14 - 17, 2009) አምስተኛ መደበኛ ጉባዔውን አካሂዶ በተሳካ ሁኔታ አጠናቋል። በዚህ ጉባዔ ላይ በተለያዩ ክፍለ ዓለማት ከሚገኙት የድርጅቱ መዋቅሮች የመጡ በርካታ ልዑካን የተገኙ ሲሆን ሰፋ ያሉ ሀገራዊና ድርጅታዊ ጉዳዮችን በጥልቀት መርምረው የሚከተሉትን ውሳኔዎች አሳልፈዋል።

1. በቅድሚያ እጅግ አስከፊና አሳሳቢ በሆነው የወቅቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ ሁኔታ ልዩ ትኩረት በመስጠት ምልዓተ ጉባዔው በጥልቀት ከመወያየቱም በላይ፣ በተለይ ሀገራችን ዛሬ ለደረሰችበት የኤኮኖሚ ድቀትና አዘቅት የገዥው ፓርቲ የህወሓት/ኢህአዴግ ጸረ-ሕዝብና ጸረ-ሀገር ፖሊሲዎች ዋነኛ ምክንያቶች መሆናቸው ተጢኗል። ሥርዓቱ ሥልጣኑን ለማሰንበት ሲል በሕዝባችን ላይ በማድረስ ላይ ያለውን ግፍና ሰቆቃን ጉባዔው በጥብቅ አውግዟል። በተጨማሪም በሥርዓቱ አራማጆች ቀጥተኛ ትዕዛዝና ተሳትፎ በቀጣይነት በመከናወን ላይ ያሉት የዜጎች ፖለቲካዊና ሰብዓዊ መብቶች መጣስ፣ መባባስና መቀጠል ሊገታ የሚችለውና የጠቅላላው የሀገሪቱና የሕዝቧ መሠረታዊ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት ሥርዓቱን በተባበረ ትግል ማስወገድ ሲቻል ብቻ መሆኑን ጉባዔው በሚገባ አስረግጧል።

2. ድርጅቱ ለፍትህ፣ ለእኩልነትና ለአንድነት በማድረግ ላይ ባለው ያልተቋረጠ ትግል በልዩ ልዩ ሁኔታዎች በህወሓት/ኢህአዴግ እጅ ወድቀው መዳረሻቸው የጠፋውን የኢሕአፓ አባላት እነ ፀጋዬ ገብረመድህንን፣ ይሥሃቅ ደብረጽዮንን፣ አምሃ በለጠን፣ ስጦታው ሁሴንን፣ አበራሽ በርታን፣ ተስፋዬ ከበደን (አባሆይን)፣ ብርሃኑ እጅጉን፣ ታምራት ግዛቸውንና ነባርና በርካታ የኢሕአፓ አባላት ሁኔታን የጉባዔው ተሳታፊዎች በመሪር ሃዘን አስታውሰው ሥርዓቱ የፖለቲካ እስረኞችን በሙሉ በአስቸኳይ እንዲፈታና ደብዛቸው የጠፉትን በይፋ እንዲያስታውቅ ጉባዔው ጠይቋል። እንዲሁም በቅርቡ በተለያየ ሰበብ ይዞ ሰብዓዊነት በጎደለው መንገድ የሚያንገላታቸውን የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር

የሆኑትን ወይዘሪት ብርቱካን ሚዴቅሳንና ከያኔ ቴዎድሮስ ካሣሁንን በአስቸኳይ እንዲፈቱ ለዚህም ያላሰለሰ የጋራ ትግል እንዲደረግ ጉባዔው ጥሪ አስተላልፏል።

3. በአሁኑ ወቅት ይበልጥ እየጎላ የመጣው ሕዝብን በሃይማኖትና በብሄረሰብ የማጋጨት እኩይና መሰሪ ተግባር ህወሓት/ኢህአዴግ ሆን ብሎ በሕዝብ ዘንድ መጠራጠሮችና አለመግባባቶችን የሚቀፈቅፍ፣ የሚያስፋፋና ለአንድነትም ሆነ በጋራና በመከባበር አብሮ መኖር ምንም ደንታ የሌለው ጸረ-ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ድርጅት መሆኑን ጉባዔው በማስረገጥ ለዘረኛውና ጠባብ ብሄረተኛው ሥርዓት ውድቀት መፋጠን የኅብረት ትግልን ማቀናጀትና ማፋፋም እንደሚገባ ለዚህም የኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) አባላት የበኩላቸውን ማበርከት እጅግ ወሳኝ መሆኑን አረጋግጧል።

4. ለሀገርና ለትውልድ መቀጠል ዋነኛ ተዋናይና ተረካቢ የሆኑት የኢትዮጵያ ወጣቶች ላይ ህወሓት/ኢሕአዴግ በረቀቀ ዘዴ የሚያደርሳቸው የሀገርን ፍቅር የመሸርሸር፣ በትውልድ አምካኝ የትምህርት ፖሊሲ የማዳከምና ተስፋ የማስቆረጥ ድርጊቶች ከምን ጊዜውም ይልቅ ይበልጥ እየተበራከቱ መምጣታቸው እጅግ ሊያሳስብና አስቸኳይ መፍትሄ የሚሻ ጉዳይ መሆኑን ጉባዔው በአንክሮ አጢኗል። ይህን ባህልን አጥፊና አዕምሮ ሰላቢ የሆነ ሥርዓት ለመለወጥ መፍትሄው ጠንክሮ መታገል ብቻ መሆኑን ጉባዔው አረጋግጧል።

5. በተመሳሳይ ሁኔታ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ግማሽ አካል የሆኑት ሴቶች ወገኖቻችን ላይ የሚደርሰው ተደራራቢ ጭቆናም መባባሱ ትኩረት የሚሻ ጉዳይና በዚህም ረገድ ትግሉ ዘርፈ-ብዙ ሆኖ መቀጣጠል እንዳለበት ጉባዔው አመልክቷል። በተለይም ደላላ ነጋዴዎች ለሴት እህቶቻችን የማይጨበጥ ተስፋ እየሰጡ ወደ ዓረብና ሌሎች አገሮች እየላኩ ከባርነት በከፋ ሁኔታ እንዲኖሩ እየተደረገ መሆኑን ገዢው ፓርቲ በትክክል እያወቀ ሁኔታው እንዲቆም አለማድረጉ ሥርዓቱ ለዜጎቹ ደንታ የሌለው መሆኑን ጉባዔው አጢኖ ድርጊቱን በጥብቅ አውግዟል። በአስቸኳይ እንዲገታም ብሄራዊ ጥሪ አቅርቧል።

6. በዲፕሎማሲ ረገድ የሚደረጉ ጥረቶች ሁሉ ይበልጥ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ከማድረግ ጋር የሲቪክ ማኅበራትና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጉልህ ሚና ይጫወቱ ዘንድ በአንድ ብሄራዊ አጀንዳ ሥር ሆነ በሌሎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሉዓላዊነትና ለሀገሪቱ አንድነት እንዲሁም ለዴሞክራሲ በተግባር በቆሙ ድርጅቶች የተጀመሩ ጥረቶችን መደገፍና ማበረታታት እንደሚገባም ጉባዔው መመሪያ ሰጥቷል።

7. ውስጣዊ ድርጅታዊ ጉዳዮችን አስመልክቶም ጉባዔው የፓርቲውን ፕሮግራም በመመርመር አሻሽሎ ያጸደቀ ሲሆን ተጨማሪ ጥናት ለሚጠይቁ ጉዳዮችም ለባለሙያ አባላቱ ሃላፊነት

ሰጥቷል። ከዚሁ ጋር የፓርቲውን ህግና የአባላት መብት መከበርን የሚከታተልና የሚያረጋግጥ ኮሚሽን አመራር አካልን ሰይሟል። በመጨረሻም ጉባዔው ድርጅቱን በከፍተኛ ሃላፊነት እስከ ቀጣዩ ጉባዔ ድረስ የሚመሩ የምክር ቤት አባላትን መርጧል።

8. የትግል ስልትን በተመለከተ ቀደም ሲል በሦስተኛው ጉባዔ በተወሰነው መሠረት ሁለገብ ትግል ትክክለኛ የትግል ስልት መሆኑን በማመን ለሠላማዊ የፖለቲካ ትግል የሚያመች ሁኔታ እንዲፈጠርም ጥረት እንዲደረግ ጉባዔው ወስኗል።

9. በቅርቡ በድርጅቱ ውስጥ በተፈጠረው መከፋፈል ምክንያት ከተለዩን አባላት ጋር ንግግርና ግንኙነት መጀመር ለትግሉ አስፈላጊ መሆኑን ጉባዔው በማመኑ ይህንን ተግባር የሚያከናውን አንድ ልዩ ኮሚቴ በአስቸኳይ እንዲቋቋም ጉባዔው አዲስ ለተመረጠው አመራር አካል ሙሉ ሃላፊነት ሰጥቷል።

10. በዚህ ጉባዔ የቀድሞ አባሎችና ደጋፊዎች የሆኑ የዴሞክራሲያዊው ትግል አጋሮች በጉባዔው ላይ በአካል በመገኘትና በቴሌኮንፍረንስ ቀርበው ለድርጅቱ ያላቸውን ድጋፍና ለሀገራቸው ያላቸውን ራዕይ በግልጽ አንጸባርቀዋል፤ ለተሰጣቸው ዕድልና አጋጣሚም ምስጋናቸውን አቅርበዋል። ከልዩ ልዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማኅበራት የተላኩ የድጋፍ ደብዳቤዎችም ተነበዋል።

11. በመጨረሻም ጉባዔው ብሄራዊና መሠረታዊ የሆኑ ሀገራዊ ችግሮቻችንን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በብቃት ለመፍታት ይረዳ ዘንድ ዛሬም የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች መተባበርና መደጋገፍ ወሳኝ መሆኑን አመላክቷል፤ የኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) አባላት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ቀረቤታ የሚረዱ ስኬታማና ተግባራዊ እገዛዎች ላይ እንዲያተኩሩና ይህንኑ ተግባራዊ እንዲያደርጉ በጥብቅ አሳስቧል። የሲቪክ ድርጅቶችም ሆኑ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በተቀናጀና በጋራ ብሄራዊ አጀንዳ ሥር አመርቂና የተባበረ ትግል እንዲያደርጉ ጉባዔው ጥሪ ከማቅረቡም በሻገር እስካሁን በኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ)ም ሆነ በሌሎች የተጀመሩ ጥረቶች መደገፍና ማበረታታት እንደሚገባቸው ጉባዔው ለአመራሩና ለአባላቱ መመሪያ ሰጥቶ በድል ተጠናቋል።

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፤

ኢሕአፓ ለሰላሳ ሰባት ዓመታት ያለመታከት የደከመበትና ገና ከጅምሩ ለፖለቲካ ትግል ያነሳሱት የሙሉ መብትና ነፃነት ጥያቄዎች እንዲሁም ለትግሉ መጧጧፍ ይረዳ ዘንድ አንግቧቸው የተነሳው መሪ ሕዝባዊ መፈክሮች ሙሉ በሙሉ ምላሽ ባለማግኘታቸው ዛሬም ድረስ በትግሉ

ቀጥሏል፤ ወደፊትም ጥያቄዎቹ ምላሽ እስኪያገኙ ድረስ ትግሉን ይቀጥላል፡፡ አለመታደል ሆኖ ሕዝባችን ለተከታታይ አምባገነን ሥርዓቶች ቢዳረግና ትግሉም መራራና እልህ አስጨራሽ ቢሆንም ለሀገርና ለሕዝብ አንድነት እንዲሁም ለእኩልነትና ለፍትህ የሚደረገው ትግል መቀጠልና ይበልጥ መፋፋም እንዳለበት ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) አጥብቆ ያምናል፤ ለተግባራዊነቱም ማናቸውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ትናንትና ከትናንት በስቲያ ለወገኑና ለሀገሩ የገባውን ቃልኪዳን በማደስና ለቆመለት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ፍጹም ተገዢ በመሆን ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ምሥረታ ዛሬም የትግል መሣሪያ ለመሆን ቃል ይገባል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ትግሉም ሆነ ድሉ የጋራ ነውና ለኢትዮጵያውያን የፖለቲካ፤ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት እንዲሁም የትግሉ ዋነኛ ባለቤት ለሆነው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዳግም የትግል ትብብር ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ያለጥርጥር በተባበረ ትግል ሕዝባችን የድል ባለቤት ይሆናል፡፡

ዛሬም እንደቀድሞው ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ተሰልፎ ይታገላል!
የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱን በትግሉ ያስከብራል!
የአንድነትና የዴሞክራሲ ኃይሎች የኅብረት ትግል ይለመልማል!
እናቸንፋለን!!

**850 Sligo Avenue Suite # 8**
**Siver Spring , MD 20910**

**P.O.Box 8141**
**Silver Spring, MD 20910**

**P.O.Box 88675**
**Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 301-578-4466 Fax: 301-449-8363 Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**